NUR AFRICA ACADEMY

የ2ኛ ክፍል የአካባቢ ሳይንስ ክለሳ



CENTER OF WISDOM

ጥቅምት 2013

ምእራፍ አራት
ክፍለ ከተማችን

4.1.የክፍለ ከተማችን መገኛ

መሰረታዊ አቅጣጫዎች

- መሰረታዊ አቅጣጫዎች የሚባሉት አራት ሲሆኑ እነሱም ሰሜንና ደቡብ ፣ ምስራቅና ደቡብ ናቸዉ ።
- የአንድን ቦታ አንጻራዊ መገኛ በስተቀኝ ፣ በስተግራ ፣ ከበስተፊት ፣ ከበስተኋላ ፣ ከላይና ከታች በማለት መግለጽ ይቻላል ።
- ክፍለ ከተማ የተለያዩ ብዙ ወረዳዎችን የያዘ የአስተዳደር እርከን ነው ።
- በአዲስ አበባ አስር ክፍለ ከተሞች አሉ ።

በክፍለ ከተማችን የሚገኙ ታሪካዊ ሥፍራዎች

- ከታሪካዊ ስፍራዎቻችን ዉስጥ
- ዋሻዎች
- አደባብዮች
- ምሽግ
- የጦር ሜዳዎችና የመሳሰሉት ናቸዉ ።
- በክፍለ ከተማችን የተለያዩ ተቋማትም ይገኛሉ ።ለምሳሌ
- በቦሌ ክፍለ ከተማ የቦሌ አለም አቀፍ አዉሮፕላን ማረፊያ ይገኛል ።
- በቂርቆስ የአፍሪካ ህብረት ጽፈት ቤት ፤ በጉለሌ ደግሞ የአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ዋና ግቢ ይገኛል ።

4.3. የክፍለ ከተማችን የመሬት ገጽታ

- የመሬት ገጽታ በአንድ አካባቢ የሚገኝ የመሬት ተፈጥሮአዊ አቀማመጥ ነዉ ።
- በአዲስ አበባ ከተማ የተለያዩ የተፈጥሮ ገጽታዎች ይገኛሉ ። እነሱም

  ሀ) ከፍተኛ የመሬት አካባቢዎች

  ለ) ዝቅተኛ የመሬት አካባቢዎች

  ሐ) ሜዳማ የመሬት አካባቢዎች ይገኙበታል ።

4.3.በክፍለ ከተማችን የሚገኙ ተቋማት

- በክፍለ ከተማችን ማህበራዊ አገልግሎት ለመስጠት የተቋቋሙ ተቋማት ይገኛል ።ለምሳሌም
- ፖሊስ ጣቢያ
- ፍርድ ቤት
- ትምህርት ቤቶች
- የጤና ተቋማት
- መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች
- የግል ተቋማትና የመሳሰሉት ናቸዉ ።

4.4 የክፍለ ከተማችን ምጣኔ ሃብታዊ እንቅስቃሴዎች

- በሁሉም ክፍለ ከተሞች ተመሳሳይ የሆነ ምጣኔ ሃብታዊ እንቅስቃሴዎች ላይኖሩ ይችላሉ ።
- ለምሳሌ ፡ - አቃቂ ቃሊቲ ክፍለ ከተማ የአዲስ አበባ ከተማ የኢንዱስትሪ ቀጠና በመሆኑ ቢዛት ያላቸዉ ኢንዱስትሪዎች ይገኙበታል ።የአቃቂ ቃሊቲ ፣ የጉለሌ፣የቦሌ ፣ የየካ ፣ የንፋስ ስልክ ላፍቶና የኮልፌ ቀራንዎ ክ ከተማዎች ደግሞ የከተማ ግብርና ምጣኔ ሃብታዊ እንቅስቃሴዎች ይገኙበታል ።

ግብርና

- ግብርና በሁለት ዋና ዋና ክፍሎች ይከፈላል ።እነሱም እርሻና ከብት እርባታ ናቸዉ ።
- በእርሻ ስራ የሚተዳደሩ ሰዎች አርሶ አደሮች ወይም ገበሬዎች ይባላሉ ።
- በከብት እርባታ የሚተዳደሩ ሰዎች ደግሞ አርብቶ አደሮች ይባላሉ ።በአዲስ አበባ ከተማ በአንዳንድ ክፍለ ከተማዎች የከተማ ግብርና ይካሄዳል

ንግድ

- ንግድ የግብርናና የኢንዱስትሪ ዉጤቶችን በሚሸጡና በሚገዙ ሰዎች መካከል የሚደረግ ልዉዉጥ ነዉ ።

መጓጓዣ

- የመጓጓዣ አይነቶች ባህላዊና ዘመናዊ ተብለዉ በሁለት ይከፈላሉ ።

የመጓጓዣ ጥቅም

- ለምጣኔ ሃብታዊ እንቅስቃሴዎች
- እቃዎችን ለማጓጓዝ
- ምርትን ለሸማቾች ለማድረስ ይጠቅማል ።

አዘጋጅ ፡ -

ማ/ር አሀመድ